# ዳግማዊ ታላቁ ሴራ!

ከሀይለ ልዑል ግርማ (ዋሽንግተን ዲሲ)

አብዛኞቻችን እንደምናስታውሰው ሁሉ የደርግ መንግስት ወድቆ ወያኔ ኢትዮጵያን ተቆጣጥሮ ሳለ አብዛኛው ኢትዮጵያዊው የወያኔን ምንነት በሚገባ ባልተገነዘበበት ወቅት "ታላቁ ሴራ" የሚል የወያኔን ገመና እና ኢትዮጵያን የማፈራረስ እቅድ የሚዘረዝር ጽሁፍ የቀድሞ ወያኔ አባሎች ከነበሩ ሰዎች ወጥቶ ስናነበው እውነት አልመሰለንም ነበር። ለአንድ ሰሞን በርካታ ወገን መጮህ ጀምሮ፣ ሰንበትበት ሲል እየተዘነጋ መጣና ምን ይደረግ ማለት ተለመደ። ቀን ውሎ ሲያድር ታላቁ ሴራም በተግባር እየተተገበረ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት በእንዴት አይነት ሁኔታ ክፍተኛ አደጋ ውስጥ እንደወደቁ በአይናችን ለማየት ቻልን። ከንፈር እየመጠጥን አንጀታችን እየጨሰ ኖርን።
ባለፉት 20 ዓመታት የተለያዩ እንቅስቃሴዎች፣ የፖለቲካ ድርጅቶች፣ ስብሰቦች፣ መድረኮች ተፈጥረው አንድ ሰሞን ዝነኛ ሆነው ትንሽ አታግለው ሲፈራረሱ ወይም ጠፍተው ሲበንኑ አይተናል። ብጭሩ አብዛኞቹ ታሪክ ሆነው ቀርተዋል። ዋናው ምክንያት ግን በአብዛኞቹ ውስጥ የወያኔና የሻዕቢያ ወኪሎችና ሰርጎ ገቦች በመግባት ብጥብጥና አለመግባባት እየፈጠሩ ነበር የሁሉም እድሜ ያጠረው። በአገር ቤትም ከግልጽ አፈናና ግድያ እስራትና ማስፈራራት ጋር ሰርጎ ገቦች ተመሳሳይ ድርጊት በመፈጸም ህዝብ የሚያምነው ድርጅት እንዲያጣ ወያኔ ያልሞከረው ሙከራ አልነበረም።

ወደ ዛሬው ርዕስ ልመለስ። ምንድነው 'ዳግማዊ ታላቁ ሴራ' ? በማን ላይ? እነማን? የሚለውን ለወገኔ ለማሳሰብና እውነተኛ አገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ ሁሉ ተረባርቦ እንዲያከሽፈው ጥሪዬን ለማቅረብ ነው።

ወያኔ በአገር ቤት ያለውን ትግል በግድያ፣ በእስራት፣ በማሰቃየት፣ ከስራ በማባረር፣ ሀብት ንብረት በመውረስ ወይም የፈጠራ ክስ መስርቶ ወንጀለኛ በማስባል በፍጹም አምባገነንና ጨካኝነት ለማፈን ቆርጦ ሲነሳ፤ እንዳፈለገው ማድረግ ያልቻለው በውጭ አገር የሚገኘውን ተቃዋሚ ክፍል ነው። ለዚህ ደግሞ መፍትሄ ያለው በ2006 አካባቢ ያወጣው ባለ 52 ገጽ መመሪያና የመደበው በሚሊዮን የሚቆጠር ዶላር እጅግ ብዙ ስራ ሰርቶለታል። በውጭ ያሉ የኤምባሲ ሰራተኞች ያንን በግዴታ ተግባራዊ ካላደረጉ ተገምግመው መውደቂያቸው የከፋ ስለሚሆንባቸው ተግተው ሲሰሩ ነው የከረሙት። አዎን ብዙዎች ፈተናውን እየወደቁ ለገንዘብ፣ ለስልጣን፤ ፤ለጥቅም ተሸነፉ። አገራቸውን በሆዳቸው በጥቅማቸው ለውጠው ያባትህ ቤት ሲዘረፍ አብረህ ዝረፍ ማለትን አዘወተሩ።

በተጨማሪም በጣም በርካታ ካድሬዎቹን በ "ተማሪ" "በሀይማኖት አገልጋይ" ስም ተቃዋሚ በሚበዛባቸው ወደ አውሮፓና ሰሜን አሜሪካ ትላልቅ ከተማዎች በመላክ ህዝቡ ውስጥ ገብተው እየከፋፈሉት፣ ግራ እያጋቡት፣ በጥቅም እየገዙት፣ ይባስ ብሎም እያስፈራሩት ይገኛሉ፡፡ ገና ከተማውን በደንብ ሳያውቁ በየእምነት ቦታዎች፤ በኢትዮጵያ ማህበር፤ በየእድሩ መግባትን በተነገራቸው መሰረት ማጥፋትን፤ መከፋፈልን፤ መበተንን ስራዬ ብለው ተያያዙት።

ሌላው እጅግ አደገኛና መሰሪ የሆነው ግራ በሚያጋባና ማመን በሚያስቸግር ሁኔታ "ሀቀኛ ተቃዋሚ" ናቸው ተብለው የሚታዩት የተቃዋሚ ድርጅት መሪዎች ነን የሚሉት፤ የህዝብን ትግል አክሽፈውና ደባ ፈጽመው እውነተኛ ታጋዩን መንገድ አስለቅቀው ቦታውን በመያዝ ካለኛም ታጋይ የለ እያሉ የወያኔን እድሜ በሌላ መንገድ ለመቀጠል እየሰሩ መሆናቸውን በሚገባ መረዳት አለብን።

## የህዝብን ትግል ከድተውና አክሽፈው ዛሬ ደግሞ ለሌላ ክህደትና ስልጣን የተሰለፉ

በዚህ መስመር የሚገኙት ከወያኔ ጋር ስልጣን ከመያዙ በፊት ጀምሮ ግንኙነት የነበራቸው፤ ወያኔም ስልጣን እንደያዘም ከያሉበት ተጠራርተው ስራና ስልጣን ይዘው ሲሞዳሞዱ፣ በገንዘብ ሲከብሩ፣ ከወያኔ ባለስልጣኖች ጋር አገር ሲያስገነጥሉና ሲያጠፉ ከርመው፤ በሁዋላ ደግሞ የህዝብ ትግል ሲጠናከር አይተው ታጋይ መስለው ገብተው ዝናና ታዋቂነት ካገኙ በሁዋላ የህዝብ ትግል ላይ ቀዝቃዛ ውሃ ቸልሰው፡ ከፋፍለው፡ ካዳከሙ በሁዋላ በወያኔ እና በውጭ መንግስታት ትእዛዝ የትግሉን አቅጣጫ አስቀይረው የፈረጠጡ ከሃዲዎች፤ አንዴ ተራራ ላይ ሆነው ባሰቡት፣ በየሬስቶራንቱ የቢራ ጠርሙስና የውስኪ ብርጭቆ ይዘው አለምንም ሀፍረት አካኪ ዘራፍ እኛ ታግለን በ6 ወር ነጻነትህን እናስገኝልሃለን አንተ ብቻ 500 ዶላር አዋጣ በማለት በውጭ የምንገኘውን በማወናበድ የተወሰነ ድጋፍ ለማግኘት ችለዋል። የተባለው ነጻነት 6 አመት አለፈው እነርሱም እንደዋሹን እኛም ዋሽንግተን ዲሲ በያለንበት ደንዝዘን ተቀምጠን ቀረን። በያመቱ የተለያየ የትግል ስልት ቀይረናል በማለት ከሰላማዊ ትግል ወደ ሁለገብ ትግል፤ ከሁለገብ ትግል ወደ ሳተላይት ቴሌቭዥን ትግል፤ ከዚያ ደግሞ ወደ ሬዲዮ ትግል፤ በዚህ ዓመት ደግሞ በደም እጁ ከተነከረውና በጸረ ኢትዮጵያዊነቱ 40 አመት ሲታገል ከቆየው ከኦሮሞ ነጻ አውጭ ግንባር (ኦነግ) ጋር ሆነን አዲሲቷን ኢትዮጵያ እንመሰርታለን ብለው እያደነቆሩን እንገኛለን። ዋናው ማደንቆሪያ መሳሪያቸው ደግሞ ‘ኢሳት’ ብለው የሚያካሂዱት የሳተላይት ቴሌቭዥን ነው። ወያኔ ‘ኢሳትን አፈነው፣ ቆረጠው’ እያሉ ምክንያት ቢያበዙም ኢሳት ለኢትዮጵያ ህዝብ የማይደርስና ጥቅም የማይሰጥ ከመሆኑም ባሻገር ስለ ወያኔ ማንነትና ምን እያደረሰበት እንዳለ ለኢትዮጵያ ህዝብ መንገር ለቀባሪው አረዱት ነው። የ’ኢሳት ቴልቪዥን በዚህ በውጭ አገር የሚኖረውን ኢትዮጵያዊ ለማደንቆርና የትግል አቅጣጫ ለማስቀየር የታቀደ ደባ መሆኑን ነው የተረዳነው። የታወቁ ኢትዮጵያውያንን በቴሌቪዥን ቃለመጠይቅ በማድረጋቸው ህዝባዊ ለመመስል ቢሞክሩም፤ ኢሳት በማን እንደተቋቋመ፤ በስንት ካፒታል እና በምን አይነት ሁኔታ እንደተመሰረተ ብዙ ጉድ እናውቃለን። በቴሌቪዥን ዜናና ቃለመጠይቅ በማቅረብ ብቻ ወያኔን ሊጥለው ወይም ሊያሰወግደው የሚችል ነገር የለም።

ድብብቆሽ በቃን እንላለን። የግንቦት ሰባት መሪዎች ነን የሚሉት እነ ዶ/ር ብርሃኑ ነጋና አንዳርጋቸው ጽጌ ያለፈው የትግል ታሪካቸው እንደሚያሳየን ለኢትዮጵያ ህዝብ ጥቅም ሳይሆን የሻዕቢያንና የወያኔን ጥቅም ሲያስጠብቁ፤ከነ ኢሳያስ አፈወርቂና መለስ ዜናዊ ጋር ውስኪ ሲያንጫልጡና ሲሞዳሞዱ፣ አገር ሲያስገነጥሉ፤ የጎሳን ፖለቲካ ሲያራምዱ፤ ለውጭ መንግስታት ትእዛዝና ፍላጎት ሲንቀሳቀሱ፤ የውጭውን ተቃዋሚ ሀይል ከፋፈለውና አዳክመው የትግሉን አቅጣጫ ሲያሰቀይሩ፤ በየስድት ወሩ የተለየየ የትግል ስልት ቀየርን በማለት ሲያወናብዱ፤ በገንዘብ ደካማ ሰዎችን በመግዛት የፈለጉትን ሲያደርጉ፤ በአፋቸው ደግሞ ጤፍ ሲቆሉ፤ የተስፋ ጮማ ሲያስቆርጡን ነው የምናውቀው። የጎሳ ፖለቲካን ከወያኔ እኩል የሚያራምዱ ልዩነታቸው እነ መለስ በስልጣን ላይ ከመሆናቸው በቀር ልዩነትም የላቸው። ግንቦት ሰባት የሚባል ድርጅት ከሰባት መሪ ነን ከሚሉ ሰዎች በቀር የድርጅት አባል የሌለው፤ በየከተማው 10 እና 15 የሚሆኑ ደጋፊዎች ሰብስቦ ተአምር ያወርድ ይመስል ግንቦት ሰባት!፣ በቃ!፣ በፌስ ቡክ አመጽ!፣ ወዘተርፈ እያሉ በመፈክር ብቻ የሚናውዙ ደካማዎች እና በሰው ጭንቅላት የሚመሩና የሚያስቡ ደላሎችን ተከትሎ ግንቦት 7 ግንቦት 7 ማለት ማለት እጅግ ደካማነትና አላዋቂነት ነው። ደጋፊ የተባሉትን መሳሪያ አድርገው አሁን ከታወቁ በሁዋላ፤ እነ ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ ከሌሎች አስቀድመው ከተዘጋጁ ግለሰቦችና ክፍሎች ጋር ወደ ዳግማዊ ሴራ እያመሩ ይገኛሉ።

EthioLion.Com

## ወንጀለኛው ወያኔ ዳግም ተመልሶ ለመምጣት ተዘጋጅቷል

አደገኛው የወያኔ መሪ ሆኖ አገር ያሰገነጠለው፡ ብዙ ንጹህ ኢትዮጵያውያንን በመግደል፣ በማሳሰር በማጥፋት ቀንደኛ የነበረውና የመከላከያ ሚኒስትር ሆኖ ከ 70000 ዜጎች በላይ በኤርትራ ድንበር ላይ ያስጨረሰው ስዬ አብርሃ ከመለስ ጋር በነበረው ግጭት የተወሰነ አመት አስሮ ስለለቀቀው ብቻ ያ ሁሉ አገር ካሃዲነቱ፣ ወገን ማስጨረሱ፣ ወንጀሉ ተረስቶ በነብርቱካን ድርጅት በኩል ገብቶ የድርጅት መሪ ሆኖ ያረፈው ወንጀለኛ ወደ ውጭም ወጥቶ በነታማኝ በየነና ሌሎች ጋሻ ጃግሬነት ተቀባይነት አይኑን በጨው  አጥቦ ለሰራው ወንጀል እንኳን የኢትዮጵያን ህዝብ ይቅርታ አልጠይቅም ብሎ ከነደሙ ከነወንጀሉ ክራባቱን አስሮ ሲንጎማለል የልብ ልብ ተሰማውና መሰሎቹን ሰብስቦ “ጠንካራ ተቃዋሚ “ ተብሎ ይኸው በድጋሚ የኢትዮጵያ መሪ ሊያደርጉት እኛው ያለንበት አሜሪካ ሀርቫርድ ዩንቨርስቲ እያሰለጠኑት ይገኛል። ዩንቨርስቲው ከለላ ሽፋን ሲሆን “አልጋ አውራሾቹ” እያዘጋጁት ይገኛል። ለምኑ? ለዳግማዊ ሴራ። ሰውየው ወያኔነት አልበቃኝም እያለ ነው። ይህ እጅግ አደገኛ እባብ የሆነ ግለሰብና ቀደም ብሎ በትምህርት ሰበብ አሜሪካ መጥቶ ድምጹን አጥፍቶ ከተደበቀው የወያኔው ጄኔራል ጻድቃን ገብረትንሳይ ጋርም እየዶለቱ ያለው ስራም ወዴት እያመሩ መሆኑን በበቂ ሁኔታ ያስረዳል። የዳግማዊ ታላቁ ሴራ መሀንዲሶች መሆናቸውን መዘንጋት በሬ ካራጁ መዋል ነው። መለስ ሊሄድ ስዬ ሊመጣ ነው! በአንድ ቢላዋ ሁለቴ ሊያርደን ተዘጋጅቷል። መታረድ ወይም መታገል የና ፈንታ ነው። ምርጫውን ለእያንዳንዳችሁ እተወዋለሁ።

## መጠቀሚያ መሳሪያ

ከምርጫ 97 በሁዋላ በግርግሩ በአቋራጭ በቀስተደመና በኩል ገብታ አባል በሆነች በ21ኛ ቀኗ በዶክተር ብርሃኑ በኩል ቀርባ የቅንጅት ም/ፕሬዚዳንት ለመሆን የበቃችው ብርቱካን ሚዴቅሳ፤ ከእስር ከተፈቱ በሁዋላ አሜሪካ መጥታ ስንቱን የዘላበደችውን ሳንረሳ፣ “ከወያኔም ላንፋታ ተጋብተናል” ብላ የቀባጠረችው እንዳለ ሆኖ፤ ወያኔ ደግሞ እንደገና ስላሰራት ብቻ በአለም ላይ የምትገኝ ልዩ ታጋይ ፍጥረት አድረገው ሲክቡዋትና ሲሸልሟት የነበረችው እርሷም እንደ አቶ ሰዬ አብርሃ “ስኮላርሺፕ አግኝታ” ለስልጠና ከመጣች ሰነበተች። በፍላጎትዋ ይሁን ተገዳ፣ ተታላም ይሁን አውቃ ጥሩ መሳሪያ መጠቀሚያ ልትሆን ከዳግማዊ ሴራ ውስጥ አለችበት። የነጋሶና መቶ አለቃ አልጋ ወራሽ ሊያደርጉዋት ሳያስቡ አልቀረም ብዙ በሀሳብ ስትነጉድ ትታያለች። በቅርቡ ሁኜ የታዘብኩት ያንን ነው።

## የአባትህ ቤት ሲዘረፍ አብረህ ዝረፍ ባዮች

በሰሜን አሜሪካ የዚሁ የዳግማዊ ሴራ አባል ለመሆን ዶክትሬትና ማስተርስ ዲግሪ ስላላቸው መንግስት መሆን የሚችሉ የመሰላቸው ጥቂት አጃቢዎችም ደፍ ደፍ ሲሉ ያታያሉ። የስደት መንግስት እያሉም ጨዋታ ይዘዋል። አንዳንዶቹም በሙያቸው ተከብረው ዝነኛ እንዳልነበሩ ሁሉ፡ በከፍተኛ የመንግስት ስራ ላይ እንዳልነበሩ ሁሉ፡ ኢትዮጵያ አስተምራ ስራ ሰጥታ፡ አክብራ፡ ወግ ማዕረግ ካዩ በሁዋላ፡ ዛሬ በስተርጅና ዘቅጠው ወርደው በደም ከተጨማለቁት ኦነግ፡ ከነሰዬ አብርሃ ጎን መሰለፋቸው ብዙዎቻችንን አሳዝኖናል። ወደፊት ስማቸውን በዝርዝር አወጣዋለሁ። እንደ አቡነ ጴጥሮስ ሰማዕት መሆን ሳይሆን እንደ አባ ጳውሎስ መዋረድና መጋለጥ ለምን እንደፈለጉ ባይገባኝም፡ ብዙዎቹ ያስተማሩኝ ሀላፊዬም የነበሩ ሰዎች ስለነበሩ ስማቸውን ከነታሪካቸው ከማውጣቴ በፊትና ህዝብ ቁሻሻ የነካው እንጨት ሳያደርጋቸው በፊት እጃቸውን እንዲሰበስቡ እመክራለሁ። በተጨማሪም ለዳግማዊ ሴራ መሳካት በተለያዩ መስክ ታዋቂ የሆኑ የኪነት ሰዎችና የሚዲያ ሰዎችን በገንዘብና በጥቅም በመያዝ ጥሩ መሳሪያ እየሆኑላቸው ነው። እነ ታማኝ በየነ ከኦነግ ጋር ሉጥ ሉጥ የሚሉት የሆድ ነገር ሆኖባቸው ሙሉ ስራቸው ይሄው ሆኖ የዳግማዊ ሴራ አቀንቀኞቻና መሳሪያዎች ሆነው እያገለገሉ ይገኛል።

EthioLion.Com

## በሻዕቢያ አስተናጋጅነት 'ኢትዮጵያን ነጻ የሚያወጡ'

ሻዕቢያ በተፈጥሮው ኢትዮጵያ የምትባል አገር እንዳትኖር ከመጣር በቀር ምንም ሌላ ስራ የሌለው ወንጀለኛ ቡድን ጸረ ኢትዮጵያ ሀይሎችን እያሰለጠነ አገራችንን ሰላም ሲያሳጣ ኖሯል። ታዲያ ዛሬም ሌላው ግራ ሲያጋባንና ሲያጃጅለን የኖረው አንሶን በተራው ደግሞ ጄኔራል ከማል ገልቹ ከአስመራ ሆኖ "ኦነግ መገንጠሉን ትቷል፣ ከኢትዮጵያ ሀይሎች ጋር ለመስራት ወሰኗል" ሲል አሜሪካ ሆነው ዕልልታውን የሚያቀልጡት እነ ብርሃኑ ነጋ ምን ለማድረግ ነው? ለመሆኑ ከማል ገልቹ ማነው? ምንስ ነበር? ከማል ገልቹ በደርግ ዘመንም በሚሊቴሪው ውስጥ የነበረ፣ ወያኔም ስልጣን ከያዘ በሁዋላ በዚያው የቀጠለና በወያኔ ተሾሞ ጄኔራል ሆኖ የክፍለጦር አዛዥ ለመሆን የበቃ 15 አመት ከወያኔ ጋር የሰራ ታማኝ ጄኔራላቸው ነበር። በ 2006 ገደማ ወያኔ በኢትዮጵያና በኤርትራ ድንበር ላይ አስቀምጦት አንድ ቀን መሸት ሸት ሲል በእግሩ እየተራመደ ሄዶ ኤርትራ የገባ ሰው ነው ያውም 150 ወታደሮች ይዞ! የወያኔን የሚሊቴሪ ሀይሉን የሚመራው ጥብቅ ቁጥጥርና በማንኛውም ቦታ የትግራይ ተወላጅ የሆነ ሰው ከላይ በማስቀመጥ መሆኑ ድፍን አለም ያውቀዋል። የከማል ገልቹ ወደ አስመራ አሊጋ በአሊጋ መንገድ ግን የሚደንቅ ነው! እንዴት ሊሆን ቻለ? ተብሎ ሲመረመር በተቀነባበር መንገድ ሚሽን ተሰጥቶት የገባ መሆኑ ሲታወቅ ዛሬ እነብርሃኑ ነጋ ኦነግ ለፈፀመው ጄኖሳይድ ተጠያቂ እንዳይሆን መከላከያ ሽፋን ሆነው ኦነግን ወደኢትዮጵያዊነት መለስን ይሉናል። የኢትዮጵያ ህዝብ ኦነግን በተገንጣይ ድርጅትነትና በወንጀለኛነት ነው የሚያውቀው። ኦነግ በጄኖሳይድ ተጠያቂ በመሆኑ፤ ከወያኔ ጋር ስልጣን ላይ በነበረበት ጊዜ ለፈጸማቸው ወንጀሎች ለፍርድ መቅረብ አለበት ነው። እነ አሊ ሀሰን የኦሮሚያ ፕሬዚዳንት በነበረበት ጊዜ፤ በአርባ ጉጉ፤ በበደኖ፤ በአርሲ፤ በወለጋ፤ በሀረር ለተጨፈጨፉት ወገኖቻችን ሰይጠየቅ ቆይቶ ነገ ደግሞ ከአትላንታ ተመልሶ ሊገዛን ሲሞክር ምን ይባላል? የኦሮሞ ህዝብ ኢትዮጵያዊ እንጂ የወንጀለኞች መደበቂያ አይደለም። ህዝብ አንቅሮ የተፋውን ተዳክሞና ተበታትኖ ሞቶ የነበረውን ኦነግ እነ ብርሃኑ ነጋ እስትንፋስ ዘርተውበትና ጉሉኮስ ምግብ ሆነው ለማቆየት የፈለጉበት ዋናው ምክንያት ለዳግማዊ ታላቁ ሴራ ዝግጅት ማሚያ አንዱ ክፍል ስለሆነ ነው። ኦነግ የሻዕቢያ ውልድ ተኮትኩቶ ያደገው በሻዕቢያ፤ መደበቂያው ሻዕቢያ መንደርደሪያው ሻዕቢያ ድጋሚ አገር እንዲያጠፋ እድል አንሰጠውም።

## ፍየል ከመድረሷ ቅጠል መበጠሷ

ቀድሞ ዩኒቲ ኮሌጅ ቀጥሎም ዩኒቲ ዩንቨርስቲ ባለቤት የነበረው ዶ/ር ፍስሀ እሸቱ ወያኔ እንደገባ አገር ቤት ገብቶ ከወያኔ ጋር ሲሰራ ቆይቶ በቅርቡ "አላሰራ አሉኝ" ብሎ ለሼህ አላሙዲን ዩንቨርስቲውን ሸጦ አሜሪካ በገባ በጥቂት ጊዜ ውስጥ "ጸረ መለስ" ሆኛለሁ እና መለስን በጥቂት ወራቶች ውስጥ ማውረድ አለብን ብሎ የስደት መንግስት አይነት አወቃቀር ያለው የሽግግር ካውንስል አቋቁመናል እና ተከተሉኝ የሚለው ሰው እጅግ ያስቃል። ስንቱ ሲያሞኘን ኖረናልና ላንተስ "ፍየል ከመድረሷ ቅጠል መበጠሷ" ብለን ከመተረት በቀር ሌላም አንልህ። ምነው አንደኛ ክፍል የነበረ ህጻን አንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን አጠናቆ ዩንቨርስቲ እስኪጨርስ ድረስ የሚፈጀውን ጊዜ አህል የመለስ መውረድ አልታየህም ነበር? ዛሬ ከምን ታየህ? አዲስ ፊት ለመቀየር ነው?ዶ/ር ፍስሃ እሸቱ የዳግማዊ ታላቁ ሴራ አካል መሆኑን በችኮላ አረጋግጧል።

EthioLion.Com

EthioLion

# ዳግማዊ ታላቁ ሴራ ምንድነው?

በአጭሩ ዳግማዊ ታላቁ ሴራ ማለት መለስ ዜናዊን በሌላ ስምና መልክ በአዳዲስ ወሮበሎችና ወንጀለኛ ድርጅቶች ለመተካት” እና መለስ ዜናዊን በፈጸመው ወንጀል ሳይጠየቅ በሰላም ሹልክ ብሎ ሂዶ የዘረፈውን ሀብት እየበላ ሲንደላቀቅ እነዚህ ‘ተቃዋሚ ነን”’ ብለው የተሰባሰቡት ግለሰቦችና ቡድኖች በኢትዮጵያ ህዝብ ጫንቃ ላይ ተቀምጠው የወያኔን የጎሳ አገዛዝ ስልት እንዳለ ሆኖ እንዲያውም በማጠናከር ከህዝበ ድጋፍ ለማግኘት ደግሞ አንዳንድ ለውጦችን አደረግን በማለት አገራችንን በውጭ ባለሀብቶች እያስበዘበዙ ሌላ ሀያና ሰላሳ የጥፋት ዘመን ለማምጣት ነው። ሀቀኛ ተቃዋሚ ድርጅቶችና አገር ወዳዱ ክፍል ተረስቶና ጠፍቶ፤ የነኦነግ፡ ግንቦት ሰባትና ከየብሄረሰቡ አንድና ሁለት ሰው ያሉት ስብስቦች “የሽግግር መንግስት ተመሰረተ” ተብሎ “ተቃዋሚው ክፍል” ስልጣን ያዘ ለማሰኘት ነው ይህ ሁሉ ደባና ሴራ! በተለይ ምሁር የተባሉት አንዳንድ ታዋቂ ሰዎች ለስልጣን ካላቸው ጉጉት ይሁን ለጥቅም ተገዝተው የዚሁ አካል ተባባሪ መሆናቸው እጅግ አሳፋሪና የወንጀለኛ ድርጅቶችና ግለሰቦች ሽፋን ከለላ መሆናቸው እንቆቅልሽ ነው አሊያም በውጭ መንግስት ፔይሮል ውስጥ ነበሬ ማለት ነው እስከዛሬ። ስም ዝርዝራቸውን ከነተግባራቸው ወደፊት ከማጋለጥ አልቀርምና ተሳስተው ከሆነ ለመታረሚያ ጥቂት ቀናቶችን እታገሳለሁ። ከዚያ ባሻገር ግን ይህን “ወያኔ ቁጥር ሁለት” የሆነውን ሴራ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ተገንዝቦ በጋራ እንደሚያከሽፈው አልጠራጠርም። ለአንዳንድ ሰዎች ደህንነት ሲባል ብዙ ሚስጥሮችን ይፋ ከማድረግ የተቆጠብኩ ሲሆን፤ ወደፊት ግን እንደ አሜሪካኑ ዊክሊክስ ይፋ ይሆናል። ይጋለጣሉ።

ኢትዮጵያዊ መንግስት በኢትዮጵያ ህዝብ ድምጽና ፍላጎት ምርጫና ድጋፍ የሚመሰረት እንጂ፤ ዶክተር ነኝ፣ ማስተርስ ዲግሪ አለኝ ወይም በዚህ ድርጅት ይህን ያህል አመት ታግያለሁና መሪ እሆናለሁ ተብሎ በውጭ አገር መንግስት ድጋፍና ቡራኬ የሚመሰረት አይደለም፡፤ይህ በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ ትልቅ ደባ፡ ትልቅ ሴራ መሸረብ ነው። የኢትዮጵያን ህዝብ መናቅ ማዋረድ ነው፤፡ የኢትዮጵያ ህዝብ አዲስ ወሮበሎችና ወንጀለኞች የሚሸከምበት ጫንቃ የለውምና፡ በኢትዮጵያም ጉዳይ ወሳኙ ህዝባችን እንጂ እንደ 91 ዓ/ም በኸርማን ኮህን ወያኔና ኦነግን “ወደፊት” የተባለው ዓይነት ድራማ ዛሬም ሊደገም ነውና፡ ዳግማዊ ታላቁን ሴራ ማክሸፍ የሀቀኛ ኢትዮጵያውያን አጣዳፊ ተግባርና ርብርቦሽ መሆን አለበት። እንደሚከሽፍም ምንም ጥርጥር የለውም። **አንድ ኢትዮጵያ፡ አንድ ሰንደቅዓላማ፡ አንድ ህዝብ!**

ዳግማዊ ታላቁ ሴራ ይከሽፋል!

ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!

ማርች 8 ቀን 2012

ዋሽንግተን ዲሲ

EthioLion.Com